# በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን
# የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት

## ከመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዝብ ክምችት ሲኖር ስለሚሰጥ ጉዞ ፈቃድ የተዘጋጀ የአሠራር መመሪያ

674/2013

መጋቢት /2005 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# መግቢያ፣

በመሳው ሀገሪቱ መደበኛነት በመርሃ-ግብር ተደገፎ እየተሰጠ ካለው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሳይ የሚኖረውን የሕዝብ ክምችትና የትራንስፖርት አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍ፣ የተጠቃሚውን ሕዝብ ፍላጐት ለማሟላትና አፈፃፀሙንም በሕጋዊ ሥርዓት ለመምራት እንዲቻል የአሰራር መመሪያ እንዲኖር ማድረግ ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል፣

ይህንኑ የትራንስፖርት የአቅርቦት እጥረትና የአሰራር ችግር በመፍታትና በግልጽ የአሰራር ሥርዓት የተሟላ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ማድረግ ልዩ ትኩረት የጠየቀበት ምክንያትም በሚፈጠረው የአቅርቦት እጥረቱ የተነሳ በተገልጋዩ ላይ የሚደርስን እንግልት ለመቀነስ፣ በዚህ እጥረትም የየትኛውም ወገን ጣልቃ ገብነት ሳይኖር በተቀመጠ ግልጽ የአሠራር ሥርዓት የተገልጋዩን ፍላጐት እንዲሟላ ለማድረግና በሥርዓት በሚመራ አግባብ አገልግሎቱን ለማስፈጸም እንዲቻል የፌደራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ይህን የልዩ ጉዞ ፈቃድ አሰጣጥና አተገባበር መመሪያ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡



## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ:-

ይህ መመሪያ በመደበኛነት በመርሐ ግብር ተደግፎ ከሚሰጠው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዝብ ክምችት ሲኖርና የአቅርቦት እጥረት ሲኖር በግልጽ በተለዩ ወቅቶች ስለሚሰጥ የሕዝብ ትራንስፖርት የልዩ ጉዞ ፈቃድ አሰጣጥና አተገባበር የወጣ የአሰራር መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጉም ፣

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እስካልተሰጠው ድረስ በዚህ መመሪያ የተጠቀሱት:-

#### 2.1. "ትራንስፖርት ባለሥልጣን"

ማለት በአዋጅ ቁጥር 468/97 የተቋቋመና የትራንስፖርት ዘርፉን ለመምራትና ለመቆጣጠር ሥልጣንና ኃላፊነቱ የተሰጠው አካል ማለት ነው::

#### 2.2. "የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች"

ማለት የክልል መስተዳድር አካላትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁር 41/85 መሰረት የክልሉን የትራንስፖርት ዘርፉ ለመምራትና ለመቆጣጠር ሥልጣንና ኃላፊነቱ የተሰጣቸው አካላት ማለት ነው::

#### 2.3. "ትራንስፖርት ማኅበራትና ድርጅቶች"

ማለት በአዋጅ ቁጥር 468/97 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 እንዲሁም አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 በፊደል ሀ እና ለ መሠረት የተደራጁና የምዝገባ ፈቃድ የወሰዱ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ማለት ነው::

#### 2.4. "የልዩ ጉዞ አገልግሎት መስጫ ጊዜ"

ማለት በመላው አገሪቱ ከሚሰጠውና በመርሐ ግብር ከተያዘው አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዝብ ክምችትና የትራንስፖርት አቅርቦት ዕጥረት የሚፈጠርባቸው ጊዜያቶች ማለት ነው::

#### 2.5. "መደበኛ ጉዞ "

ማለት በመሳው አገሪቱ በመደበኛነት በመርሐ ግብር ተደግፎ የሚሰጥ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ማለት ነው።

## 2.6. *"የልዩ ጉዞ መርሐ ግብር"*

ማለት ሁሉም አገልግሎት ሰጪ ትራንስፖርት ማኅበራትና ድርጅቶች ከመደበኛው ትራንስፖርት አገልግሎት ውጪ በሆኑና ባሏቸው አባል ተሽከርካሪ በዚህ መመሪያ በግልፅ በተለዩና የል ጉዞ ፈቃድ በሚሰጥባቸው ጊዜያትና የጉዞ አቅጣጫ ለሚሰጥ ፈቃድ የሕዝብ ትራንስፖርት የልዩ ጉዞ አገልግሎት መፈጸሚያነት የሚዘጋጅ የሥምሪት ኘሮግራም ማለት ነው።

## 2.7. *"የልዩ ጉዞ አገልግሎት መስጫ ቦታ"*

ማለት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ታስቦ የተዘጋጀ መናኸሪያ ማለት ነው።

## 2.8. *"የዲስኘሊን ቅጣት"*

ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የልዩ ጉዞ አገልግሎት ለመስጠት መርሐ ግብር ወጥቶላቸው አገልግሎት ያልሰጡ ትራንስፖርት ማኅበራትና ድርጅቶች፣የተሽከርካሪ ባለንብረቶች አሽከርካሪዎችና ሙያተኛ ሠራተኞች ላይ የሚወሰድ የዲስኘሊን ቅጣት ማለት ነው።

## 2.9 *"የልዩ ጉዞ ሥምሪት ማረጋገጫ ፈቃድ"*

ማለት በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን በክልል ትራንስፖርት አካላት አማካይነት ትራንስፖርት ማኅበራትና ድርጅቶች በሚሰጡት የሥምሪት ፈቃድ ላይ የሚደረግ ማረጋገጫ ማለት ነው።

# 3. *የልዩ ጉዞ አገልግሎት ስለመስጠት:-*

በመሳው ሀገሪቱ በመደበኛነት በመርሐ ግብር ከሚሰጠው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዝብ ክምችና የትራንስፖርት ዕጥረት በሚኖርባቸው ጊዜያቶችና የጉዞ መስመሮች ብቻ በሚወጣለት የድርጊት መርሐ ግብር መሰረት መደበኛውን አገልግሎት እንዳበቃ በፍላጐት (ፈቃደኝነት) ከሚደረግ ጉዞ በኋላ በአስፈፃሚ አካላት ቁጥጥርና በአገልግሎት ሰጪዎች ሙሉ የተግባር ተሣትፎ በአገልግሎት መስጫ መናኸሪያ ውስጥ የልዩ ጉዞ አገልግሎት ይሰጣል።

# 4. *የልዩ ጉዞ ፈቃድ የሚሰጥባቸው ወቅቶች:-*

በሀገሪቱ ሕዝቦች በሚከበሩ ሕዝባዊና ኃይማኖታዊ በዓላት እንዲሁም በልዩ ሁኔታ በሚታዩና በመደበኛነት ከሚሰጠው የትራንስፖርት አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዝብ ክምችትና የአቅርቦት እጥረት የሚኖረትባቸውና የልዩ ጉዞ አገልግሎት መስጠት የሚኖርባቸው ጊዜያትችና ቦታዎችን በተመለከተ ቀጥሎ በተዘረዘረው መልኩ ያሉትን ይመለከታል፡፡

## 4.1 *ልዩ ልዩ በዓላት ቀናት፣*

| ተ.ቁ | ከመደበኛ አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዝብ ክምችትና የትራንስፖርት አቅርቦት እጥረት ያለባቸው ወቅቶች | እጥረቱ የሚጉላባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች /ቦታዎች/ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዘመን መለወጫ | በሁሉም ክልል መስተዳድር ከተሞች | |
| 2. | መስቀል በዓል | በደቡብ ክልል ( በጉራጌ፣ ሐድያ፣ ከንባታ ፣ወላይታና ጋሞጎፋ ዞንና አካባቢዎች)፣ | |
| 3. | ገና በዓል | በአማራ ክልል (ላሊበላና አካባቢው) | |
| 4. | ጥምቀት በዓል | በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች (ዋንኛነትም በጎንደር፣ ጎጃምና ባሕርዳር ) | |
| 5. | ፋሲካ በዓል | በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ክልሎች አካባቢ | |
| 6. | አረፋ | ከደቡብ ፣ ኦሮሚያና አማራ ክልል (በጉራጌ ዞን፣ በጅማ ዞንና ደሴ ዞን )፣ | |
| 7. | ፈረቀሳ | በኦሮሚያ ክልል ባሌና አርሲ አካባቢ፣ | |
| 8. | ሼክ ሁሴን | በኦሮሚያ ክልል ባሌና አካባቢው፣ | |
| 9. | እሬቻ /ሆራ | በኦሮሚያ ክልል ( ቢሾፍቱና አካባቢው)፤ | |

### 4.2 *ትኩረት የሚሹ ወቅቶች፣*

| ተ.ቁ | የሕዝብ ክምችት የሚኖርባቸው | አቅርቦት የሚጠይቁ እና ዕጥረት የሚኖርባቸው ቦታዎች | ምርመራ |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ወቅቶች | | |
| 1. | በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት /ዩኒቨርስቲዎች/ የተማሪዎች መግቢያ ጉዞ ወቅት፤ | ⏭ በየዓመቱ ከመስከረም እስከ ጥር ባሉት ወራት፤<br>⏭ የትምህርት ተቋማት በሚኖራቸው የእረፍት ጊዜያት በሚደረጉ ጉዞዎች ወቅት፤ | |
| 2. | በመላው ሀገሪቱ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግር ሲኖርና ከፍተኛ የትራንስፖርት አቅርቦት በሚኖርባቸው ጊዜያት፤ | ሁኔታዎችን ተከትሎ አቅርቦት በሚፈልግበት ጊዜያት:-<br>⏭ የመከላከያ ልዩ ጉዞ፤<br>⏭ የተፈጥሮ አደጋና ሌሎች ችግሮች ሲኖሩ፤ | |

## 5. "ስለ ልዩ ጉዞ ፈቃድ አሰጣጥ:-

ከመደበኛ አገልግሎት በላይ የሕዝብ ክምችት ሲኖርና የትራንስፖርት አቅርቦት እጥረት ሲኖር በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ 4.1 መሠረት ለተለዩት ጊዜያቶች ከዚህ በሚከተለው የልዩ ጉዞ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ደረጃ በደረጃ ተፈጻሚ ይደረጋል:-

5.1 ያለውን የአቅርቦት ዕጥረት ለማሟላት በራስ ተነሳሽነትና ፍላጐትና በገንባር ቀርበው በመደበኛ አሰራር አገልግሎት ለመስጠት ለሚጠይቁ ትራንስፖርተሮች ቅድሚያ ፈቃድ እንዲያገኙና ወደጠየቁበት የጉዞ መስመር እንዲሰማሩ ይደረጋል፤

5.2 በመቀጠልም የሚኖረውን የሕዝብ ክምችትና የአቅርቦት እጥረት በመደበኛነት ካልተሸፈኑና ለውድድር ተመላሽ ከሚሆኑ የጉዞ መስመሮች ማካካሻ ለማገኘት ፈቅዶ በመደበኛ የጉዞ ታሪፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ትራንስፖተሮች ቀጣይ ፈቃድ በመስጠት ማሰማራት።

5.3 በመቀጠልም 35 ፐርሰንት የመደበኛ ጉዞ ክፍያ ታሪፍ ጭማሪ በማድረግ አገልግሎት ለመስጠት ለሚፈልጉ ትራንስፖርተሮች ቅድሚያ ፈቃድ እንዲሰጥ በማድረግ።

5.4 በየደረጃው በተሰጡ ፈቃዶች ያሰው የአቅርቦት ችግር ካልተፈታ በመደበኛ ታሪፍ ላይ 50 ፐርሰንት ተጨማሪ በማድረግ አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ ደረጃውን በጠበቀ የፈቃድ አሰጣጥ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡

## 6. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ጉዞ ወቅት የልዩ ጉዞ ፈቃድ አሰጣጥመና አፈጻጸም፣

ከመደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የአቅርቦት መጠን የሚጠይቅ በመላው አገሪቱ በሚገኙ ከፍተኛ የትምሕርት ተቋማት የተማሪዎች እንቅስቃሴ በሚኖርበት ጊዜ ይህንኑ ከፍተኛ ፍላጐት ለማሟላት በትምህርት ሚኒስቴር በሚቀርብ መረጃ መሠረት በመደበኛ በሚሰጠው አገልግሎት ከሚደረግ ሙሉ የማጓጓዝ ሥራ ጎን የልዩ ጉዞ ፈቃድ ከዚህ በሚከተለው የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ደረጃ በደረጃ ተፈጻሚ ይደረጋል፡-

6.1 ተማሪዎችን በመደበኛ ታሪፍ ለማጓጓዝና የመስመር ማካካሻ በማግኘት አገልግሎት ለመስጠት ለሚፈልጉ ሁሉ ቅድሚያ የጉዞ ፈቃድ አግኝተው እንዲሰወማሩ ይደረጋል፡፡፤

6.2 ከማካካሻ ጉዞ ፈላጊ ውጭ በተጨማሪ ክፍያ ለመስራት የሚፈልጉ ካሉም ቀጣይ የጉዞ ፈቃድ ከመደበኛ የሥራ ደረጃ ታሪፍ 35% ( ሰላሳ አምስት ፐርሰንት የዋጋ ጭማሪ) በማድረግ አገልግሎት ለመስጠት ለሚቀርቡ ቀጣይ የልዩ ጉዞ ፈቃድ ይሰጣል፤

6.3 የአገልግሎት አቅርቦቱ እስካልተቃለለ ድረስም ከመደበኛ የሥራ ደረጃ ታሪፍ 50% ( ሃምሳ ፐርሰንት የዋጋ ጭማሪ) በማድረግ አገልግሎት ለመስጠት ለሚቀርቡ በመጨረሻ ደረጃ የልዩ ጉዞ ፈቃድ በመስጠት አገል4ግሎት እንዲኖር ይደረጋል፤

6.4 ከላይ የተዘረዘሩት የልዩ ጉዞ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደቶች እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አገልግሎት አሰጣጥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ትራንስፖርት ማኅበራትና ድርጅቶች በጋራ በሚደርሱበት የሥራ ስምምነት መሰረት የሚፈፀም የሥራ ስምምነት ሲኖርም ከአገልግሎት ሰጪው በሚቀርብ መረጃ መሠረት አስፈጻሚ አካላት የልዩ ጉዞው እንዲፈጸም ማረጋገጫ በመስጠት አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

## 7. ከመንግስት ስለሚጠየቁ የልዩ ጉዞ አገልግሎቶች በተመለከተ ፡-

በመላው ሐገሪቱ የሚፈጠርን ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ችግር መሰረት በማድረግ መንግስት በሚኖረው የትራንስፖርት አቅርቦት ፍላጎት መሰረት ስለሚሰጥ የል ጉዞ አገልግሎቶች ጥያቄ

አቅራቢውና አገልግሎት ሰወጪው በሚደርሱበት የሥራ ስምምነት መሰረት ተፈላጊው አቅርቦት እንዲሟላና አገልግሎት በወቅቱ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

## 8 *"የልዩ ጉዞ አገልግሎት ታሪፍን በተመለከተ፡-*

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 በንኡስ አንቀጽ 4.1 እና 4.2 በዝርዝር በተገለፁት የልዩ ጉዞ አገልግሎት ሲሰጥባቸው በሚገቡ ጊዜያቶችና የጉዞ አቅጣጫዎች የሕዝብ ተሽከርካሪዎችም እየሰጡ ባሉበት የሥራ ደረጃ መሠረት ሁሉም አገልግሎት ሰጪዎች በመደበኛ አገልግሎት በሚያስከፍሉት ታሪፍ መነሻነት በተቀመጠው የአሰራር መመሪያ ሥርዓት የፐርሰንት ክፍያ ተመኑን ተገልጋዩን ሕዝብ በማስከፈል የሚያጓጉዙ ሲሆን በዚህ ሂደትም ውስጥ በአገልግሎት አሰጣጡ በመደበኛ የጉዞ መመሪያ በተቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ መሠረት ተፈጻሚ የሚደረግ ሆኖ ፡-

6.1 7 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት ምንም አይነት ክፍያ አለመቀበል፤

6.2 ከ7 ዓመት እስከ 12 ዓመት ላሉ ሕፃናት በመደበኛ የአገልግሎት ክፍያ ተመን ታሪፍ ጥማሪውን ተከትሎ ግማሽ ክፍያ እንዲፈጸም በማድረግ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 9. *የጉዞ መርሃ- ግብር ስለማዘጋጀት፣*

ከላይ በመመሪያው አንቀጽ 4 በንዑስ አንቀጽ 4.1 እና 4.2 በተዘረዘሩ ጊዜያቶች የጉዞ ቦታዎች የሚኖረውን የሕዝብ ክምችትና የትራንስፖርት አቅርቦት እጥረት ለመፍታት በመደበኛ ፕሮግራም እንዲሰጡ ከሚመደቡ ተሽከርካሪዎች ውጭ ሁሉም አባል ተሽከርካሪዎች የል ጉዞ የሚፈጽሙበት መርሐ ግብር ከበዓሉ በፊት ባሉ 15 ቀናት ውስጥ በትራንስፖርት ማሕበራትና ድርጅቶች ተዘጋጅቶ ለአስፈጻሚው አካል መቅረብ መጽደቅ አለበት፡-

## 10. *የልዩ ጉዞ አገልግሎትን ስለመስጠት፡-*

ማንኛውም በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የተሠማራና የሥራ አቅምና ደረጃ በሚፈቅድለት መሰረት የተደራጀ ትራንስፖርተር በተደራጀበት ማኅበር ወይም ድርጅት አማካይነት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ 4.1 እና 4.2 በግልፅ በተለዩ ጊዜያቶች የጉዞ ቦታዎች ለሚሰጥ የልዩ ጉዞ አገልግሎቶች በተዘጋጀው መርሐ ግብር መሠረት በመናኸሪያ በመገኘት የጉዞ ቅደም ተከተል እና የሥራ ተራን በመጠበቅ ሁሉም ትራንስፖርተር የተሟላ አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ሁለት

## በልዩ ጉዞ አገልግሎት አፈፃፀም የአስፈፃሚ አካላትና ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 11. የአስፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት:-

በመሳው አገሪቱ ከሚሰጠው መደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዘብ ብዛትና የትራንስፖርት ዕጥረት በሚታይባቸውና በመመሪያው አንቀጽ 4 በተዘረዘሩት ጊዜያች በሚሰጡ የልዩ ጉዞ አገልግሎት ወቅት በየደረጃው ያሉ አስፈፃሚ አካላት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖርባቸዋል::

### 11.1 የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት:-፣

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ 4.1 እና 4.2 በተገለጹት ጊዘዬቶች ከመደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዘብ ክምችትና የትራንስፖርት ዕጥረት በሚኖርባቸው ጊዜያቶች ችግሩን ለመፍታት እንዲቻል ትራንስፖርት ማኅበራትና ድርጅቶች ወቅቱን የጠበቀ

የልዩ ጉዞ መርሐ ግብር እንዲያቀርቡ ያደርጋሉ፣ መርምሮ በማጽደቅ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጓል፣

2. ትራንስፖርት ማሕበራትና ድርጅቶች ስልዩ ጉዞ የሥምሪት መርሐ ግብር ወቅቱን ጠብቆ ካላዘጋጁና ካላቀረቡም አገር አቋራጭ አውቶብሶችን በተመለከተ ከመደበኛ ፕሮግራም ውጭ የሆኑትን ባካተተ መልኩ የሥምሪት መርሐ ግብር በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጓል፡፡

3. እጥረቱን ተከትሎ በግልጽ በተለዩት ጊዜያቶችና ቦታዎች የልዩ ጉዞ አገልግሎት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት መደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በመርሐ ግብር መሰረት በተሟላ መልኩ እንዲፈጸም ማድረግ፣

4. ከመደበኛ አገልግሎት በኋላ ያለውን የሕዝብ ክምችት ለማቃለልም በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 5 6 እና 7 መሰረት የልዩ ጉዞ ፈቃድ አሰጣጥና አፈጻጸም በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሰረት መፍቀድ፣

5. በመመሪያው መሠረትም ስልዩ ጉዞ የተመደቡ ተሽከርካሪዎች የጉዞ ዝግጅታቸውን እንዳጠናቀቁ በማረጋገጥና ተገቢውን ቁጥጥር በማድረግ ስለጉዞው ሕጋዊነት ማረጋገጫ ፈቃድ በመስጠት ማስማራት፡፡

6. በልዩ ጉዞ መርሐ ግብር የተመደቡ ተሽከርካሪዎች እንዲሠማሩ በተዘጋጀው ጉዞ መስመር ተሣፋሪ ከሌለና በሌሎች ጉዞ መስመሮች ተጨማሪ አቅርቦት ካስፈለገም ተገልጋይ ወደ በብዛት ወዳለበት የጉዞ መስመር እንዲሠማሩ ማድረግ፡፡

7. በነዚህ ጊዜያቶች በመደበኛም ሆነ በልዩ ጉዞ ተመደበው አገልግሎት ያልሰጡና ኃላፊነታቸው ያልተወጡ ተሽከርካሪዎችን በመረጃ በመለየትም የሚሠሩበትን ማኅበር /ድርጅት/ የተሽከርካሪውን ባለንብረትና የተሽከርካሪ አሽከርካሪዎችን በተመለከተ በተሻሻለው አገራዊ የሕዝብ ትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ የሥምሪት አፈጻጸም መመሪያ ስለዚሁ የሥራ ክንውን ጥፋትና የቅጣት እርምጃ አወሳሰን በግልፅ በተቀመጠው መሠረት የቅጣት እርምጃ መውሰድ፣

8. በልዩ ጉዞ ስለተሰጡ አገልግሎቶችና አፈፃፀም እንዲሁም ስለተወሰዱ የዲስፕሊን ቅጣቶች ተገቢውን የሥራ መረጃ በማደራጀትና ስይቶ መያዝ፡፡

9. መመሪያውን ተፈጻሚ ስለመሆኑ ተገቢውን የሥራ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

10. የአገልግሎት አሰጣጡን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግም ግምገማ ማድረግና በየጊዜው ማስተካከያ እንዲወሰድበት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## 11.2 የክልል መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮዎች ተግባርና ኃላፊነት፡-

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ 4.1 እና 4.2 በተገለጹት ጊዜዎች ከመደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዘብ ክምችትና የትራንስፖርት ዕጥረት በሚኖርባቸው ጊዜያቶች ችግሩን ለመፍታት እንዲቻል ትራንስፖርት ማኀበራትና ድርጅቶች ወቅቱን የጠበቀ የልዩ ጉዞ መርሐ ግብር እንዲያቀርቡ ያደርጋሉ፤ መርምሮ በማጽደቅ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጓል፤

2. ትራንስፖርት ማሕበራትና ድርጅቶች ለልዩ ጉዞ የሥምሪት መርሐ ግብር ወቅቱን ጠብቆ ካላዘጋጁና ካላቀረቡም የመስስተኛና አነስተኛ ሕዝብ ማመላለሻዎችን በተመለከተ አደራጁ የክልል ትራንስፖርት አካል ከመደበኛ ፕሮግራም ውጭ የሆኑትን ባካተተ መልኩ የሥምሪት መርሐ ግብር በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጓል፡፡

3. እጥረቱን ተከትሎ በግልጽ በተለዩት ጊዜያቶችና ቦታዎች የልዩ ጉዞ አገልግሎት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት መደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በመርሐ ግብር መሰረት በተሟላ መልኩ እንዲፈጸም ማድረግ፤

4. ከመደበኛ አገልግሎት በኋላ ያለውን የሕዝብ ክምችት ለማቃለልም በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 5 6 እና 7 መሰረት የልዩ ጉዞ ፈቃድ አሰጣጥና አፈጻጸም በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሰረት መፍቀድ፤

5. በመመሪያው መሠረትም ለልዩ ጉዞ የተመደቡ ተሽከርካሪዎች የጉዞ ዝግጅታቸውን እነዳጠናቀቁ በማረጋገጥና ተገቢውን ቁጥጥር በማድረግ ለስጉዞው ሕጋዊነት ማረጋገጫ ፈቃድ በመስጠት ማሰማራት፡፡

6. በልዩ ጉዞ መርሐ ግብር የተመደቡ ተሽከርካሪዎች እንዲሠማሩ በተዘጋጀው ጉዞ መስመር ተሣፋሪ ከሌለና በሌሎች ጉዞ መስመሮች ተጨማሪ አቅርቦት ካስፈለገም ተገልጋይ ወደ በብዛት ወዳለበት የጉዞ መስመር እንዲሠማሩ ማድረግ፡፡

7. በነዚህ ጊዜያቶች በመደበኛም ሆነ በልዩ ጉዞ ተመድበው አገልግሎት ያልሰጡና ኃላፊነታቸው ያልተወጡ ተሽከርካሪዎችን በመረጃ በመለየትም የሚሠሩበትን ማኅበር /ድርጅት/ የተሽከርካሪውን ባለንብረትና የተሽከርካሪ አሽከርካሪዎችን በተመለከተ በተሻሻለው አገሪዊ የሕዝብ ትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ የሥምሪት አፈጻጸም መመሪያ ለስዚሁ የሥራ ክንውን ጥፋትና የቅጣት እርምጃ አወሳሰን በግልፅ በተቀመጠው መሠረት የቅጣት እርምጃ መውሰድ፤

8. በልዩ ጉዞ ስስተሰጡ አገልግሎቶችና አፈፃፀም እንዲሁም ስስተወሰዱ የዲስኘሊን ቅጣቶች ተገቢውን የሥራ መረጃ በማደራጀትና ሰይቶ መያዝ::

9. መመሪያውን ተፈጻሚ ስስመሆኑ ተገቢውን የሥራ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣

10. የአገልግሎት አሰጣጡን ይበልጥ ውጤታማ ስማድረግም ግምገማ ማድረግና በየጊዜው ማስተካከያ እንዲወሰድበት ማድረግ ይጠበቅበታል::

## 11.3 *የትራንስፖርት ማኅበራትና ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት:-፣*

1. በመደበኛነት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚሰጡ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቶች የሕዝብ ክምችት በሚኖሩባቸው ወቅቶች ተሟልተው እንዲሸፈኑና አገልግሎት እንዲሰጥባቸው በአባል ተሽከርካሪዎቻቸው ላይ ተገቢው የሥራ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋሉ፤

2. ከመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በላይ የሚኖርን የሕዝብ ክምችትና የሚፈስገውን ትራንስፖርት አቅርቦት ስማሟላት እንዲቻል በትራንስፖርተሮች አማካኝነት ስስሚሰጥ የልዩ አገልግሎት ፈቃድ አፈፃፀም በመመሪያው አንቀፅ 5 አንቀፅ 6 እና 7 መሠረት አገልግሎት እንዲሰጥ ጥያቄ ያቀርባሉ ያስፈፅማሉ፤

3. የሕዝብ ክምችትን ተከትሎ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 4.1. እና 4.2. መሠረት አገልግሎት በሚሰጥባቸው ጊዜያትችና የጉዞ መስመርች ስአባል ተሽከርካሪዎቻቸው የጉዞ መርሐ ግብር ያወጣሉ አፈፃፀሙንም ይከታተላሉ፤

4. ስስሚሰጡ የልዩ ጉዞ ፈቃድ አገልግሎቶች የወጡትን መመሪያዎች ተፈፃሚነት በመከታተልና በመቆጣጠር የበኩላቸውን ድርሻ ይወጣሉ፤

5. የልዩ ጉዞ ፈቃድ አገልግሎትን በተመስከተ የተሟላ መረጃ በማደራጀትና በአፈፃፀሙም የአሠራር ክፍተት ወይም የዲስኘሊን ጥፋት የሚፈጽሙትን በሕግና ሥርዓት እንዲሰሩ ስማድረግ ንቁ ተሳትፎ፣

## 11.4 *የባለንብረቶች (ትራንስፖርተሮች) ተግባርና ኃላፊነት፣*

1. በመደበኛ መርሐ ግብር የሚሰጡትን አገልግሎት እንዲሁም ሁሉ በነዚህ ጊዜያቶች ውስጥ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ተግባራዊ ማድረግ፤

2. የልዩ ጉዞ አገልግሎቶች እንዲሰጡ በተመደቡበት የጉዞ መስመር በሚሰጣቸው የሥምሪት ተራ መሠረት በወቅቱ ተገኝቶ አገልግሎት መስጠት፤

3. ከዚህ መመሪያ ውጭ የተሰጣቸውን የጉዞ ሥምሪት ሳይወጡ ሌላ የጉዞ ሥምሪት ስማድረግ አስመሞከር፤

4. ስሚመደቡበት የልዩ ጉዞ አገልገሎት መርሐ ግብር መሠረት በወቅቱ በመገኘት ከፌዴራልና ክልል ትራንስፖርት ቢሮ የሥራ ፈቃድ በመውሰድ ተግባራዊ ማድረግ፤

5. ከመመሪያው ከተዘረዘሩት ጊዜያት ውጭ የልዩ ጉዞ አገልግሎት በሚል በተገልጋዩ ሳይ አሳስፈሳጊ ጫና ስመፍጠርና አገልግሎት ስመሰጠት ከሚደረግ ሕገወጥ ተግባር መቆጠብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 11.5 *አሽከርካሪዎች:-*

1. በመመሪያው በግልፅ በተዘረዘሩ ጊዜያቶች የልዩ ጉዞ አገልግሎት እንዲሰጡ በመርሐ ግብር በተመደቡበት የጉዞ መስመር አገልግሎት መስጠት፤

2. በነዚህ ጊዜያቶች የሚኖርን የሕዝብ እንግልት ስመቀነስና በሥርዓት ስማገልገል እንዲቻል ከልዩ ጉዞ መርሐ ግብር ውጭም በመደበኛ የጉዞ ሥምሪት የተመደቡበትን መስመር አክብር ተገቢ አገልግሎት መስጠት፤

3. አገልግሎት የሚሰጡበትን ተሽከርካሪ በወጣው መርሐ ግብር ብቻ በሚመደቡበት መናኸሪያ ውስጥ የሚሰጣቸውን የጉዞ ተራ ጠብቆ በመግባትና ወደ ተመደቡበት ጉዞ መስመር የሥራ ማረጋገጫ ፈቃድ ወስዶ መሥራት፤

4. ከመመሪያው ውጭ ሌላ ሁኔታ ፈጥሮና ተጠቅሞ በሕገወጥነት ወደ የትኛውም ጉዞ መስመር ስመንቀሳቀስ ከመሞከር መቆጠብና ስሥርዓት ተገዥ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 11.6 *ተገልጋዩ ሕዝብ:-*

በመሳው ሃገሪቱ ከሚሰጠውና በመርሐ ግብር ከሚከናወነው መደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ውጭ በመመሪያው በተቀመጡ ጊዜያቶች ውስጥ:-

1. አቅርቦት በሚዘጋጅባቸው መናኸሪያዎች በመገኘት በልዩ ጉዞ በሚመደቡ ተሽከርካሪዎች መጠቀም፤

2. የሚሰጡ የልዩ ጉዞ አገልግሎቶች በየመናኸሪያው ባሉ አካላትና በዚህ መመሪያ መሠረት መፈፀሙን ማረጋገጥና ካልሆነም የሚገጥማቸውን ችግር አሳውቀ መፍትሄ ማገኘት፤

3. ወደ ሚሄደበት የጉዞ መስመር ለሚመደቡ ተሽከርካሪዎች በሥርዓት ገብተው ወደ ጉዞአቸው እንዲሄዱ የጉዞ ተራ ይዞ በመጠቀም የጊዜ ብክነት እንዳይፈጠር ትብብር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 11.7 ትምህርት ሚኒስቴር:-

1. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀፅ 4.2. በግልፅ በተቀመጠው መሠረት በመላው ሀገሪቱ የሚኖረውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጉዞ እንቅስቃሴ በተመለከተ የሚፈለገውን አገልግሎት መስጠት እንዲቻል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በየደረጃው ካሉ የፌዴራልና የክልል የዘርፉ አካላት ጋር በመመካከር ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለጓጓዙ ተማሪዎች የሚኖረውን የጉዞ ፍላጐት መሠረት በማድረግ:-

2. የጉዞ ቦታዎችን የጉዞ ወቅትና የተጓዥ መጠን በመለየት አገልግሎቱ ሊሰጥ የሚችልበትን አማራጭ ቦታ ወይም ከመደበኛ የአገልግሎት መስጫ መናኸሪያ ሲፈፀም ስለመቻሉ በግልፅ በመለየት ጉዞው ከሚጀመርበት 15 ቀናት በፊት ለፌዴራል ወይም ለክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ማሳወቅ ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግበት በማድረግ፤

3. ያለውን ፍላጐት መሠረት ባደረገ አግባብ ዝርዝር መረጃ አስቀድሞ በመላክና በማሳወቅ በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ክልል ቢሮዎች አማካይነት ከአገልግሎት ሰጪ ትራንስፖርት ማኅበራትና ድርጅቶች ጋር የሥራ ስምምነት ላይ በመድረስ አገልግሎቱ በተሟላ አገቦብ እንዲሰጥ ማድረግ ይችላል፡፡

## ***<u>ክፍል ሦስት</u>***

## ***<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>***

### 12. ***<u>የልዩ ጉዞ መርሐ ግብር አዘገጃጀት፣</u>***

ከመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዝብ ከፍምትና የትራንስፖርት ዕጥረት በሚያጋጥምባቸውና በዚህ መመሪያ በግልፅ በተዘረዘሩ ጊዜያቶች ውስጥ ትራንስፖርት ማኅበራትና ድርጅቶች በቋሚነት ከሚያወጡት መርሐ ግብር በተጨማሪ ለልዩ ጉዞ አገልግሎት የሚያገለግል በመመሪያው ለተገለጹ ጊዜያት የሚውል የሥምሪት መርሃ-ግብር ያዘጋጃሉ:: ሰነዱ በወቅቱ ተዘጋጅቶ ካልቀረበም አስፈጻሚ አካላት በራሳቸው አዘጋጅተው ማስፈጸም ይችላሉ::

### 13. ***<u>የመርሐ ግብር ሰነድ ይዘት፣</u>***

ከመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በላይ የሚፈጠርን የተገልጋዩ ሕዝብ ክምችትና የትራንስፖርት አቅርቦት ዕጥረት ተከትሎ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ 4.1 እስከ 4.2. በግልጽ በተለዩ ጊዜያቶች በቋሚነት አገልግሎት በሚሰጡ ትራንስፖርት ማኅበራትና ድርጅቶች የሚዘጋጀው የልዩ ጉዞ አገልግሎት መርሐ ግብር በመደበኛ የሚመደቡትን አባል ተሽከርካሪዎች በመለየት፣ በመደበኛ የጉዞ ሥምሪት ኘሮግራም ያልተካተቱትን ተሽከርካሪዎች ሙሉ ለሙሉ በልዩ ጉዞው በማካተት፣ ሲኖር የሚችለውን የትራንስፖርት ተጠቃሚ ሕዝብ ፍላጐትና መጠን በማገናዘብ፣ የሚመደቡትም ተሽከርካሪዎች የተገልጋይ ፍላጎት እንዲያሟሉ ተደርጎ መዘጋጀት አለበት::

## 14. በልዩ ጉዞ የመሳተፍ መብት ስለማግኘት ፣

ከመደበኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በላይ የሚፈጠርን የሕዝብ ክምችትና የትራንስፖርት ዕጥረት ተከትሎ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ 4.1 እስከ 4.2. በገልጽ በተለዩ ጊዜያቶች ለሚሰጥ የልዩ ጉዞ አገልግሎት የሥምሪት ክልል ገደብ ሳይደረግ የጉዞ ርቀት ተጠብቆ ሁሉም አገልግሎት ሰጪ በመረጠው አቅጣጫ የአገልግሎት ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችለውን መርሐ-ግብር መንደፍና አቅርቦ በማጸደቅ ተግባራዊ ማድረግ ይችላል፡፡ አስፈጻሚ አስካላትም የቀረበውን መርሃ-ግብር ይዘት መርምረው በማጽደቅ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

## 15. መርሃ-ግብር በማጸደቅ ሥራ ላይ ማዋል፣

መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዝብ ክምችትና ትራንስፖርት ዕጥረት በሚኖርባቸውና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ 4.1 እስከ 4.2 በተለዩ ጊዜያቶች ለሚሰጥ የልዩ ጉዞቸደ አገልግሎት ትራንስፖርት ማሕበራትና ድርጅቶች፡-

15.1 ጊዜው ከመድረሱ 15 ቀናት በፊት ያላቸውን አባል ተሽከርካሪዎች ያካተተ መርሐ ግብር በየጉዞ መስመሩ በመመደብ የሥምሪት ፕሮግራም ያዘጋጃሉ፣

15.2 በዚህ መርሃ-ገብር ውስጥ በመደበኛ አገልግሎት ለጭነት የራሳቸው ፕሮግራም ያላቸው ተሽከርካሪዎች እንዳይካተቱ ይደረጋል፣

15.3 በተዘጋጀው የልዩ ጉዞ መርሃ-ግብርም በየደረጃው ባሉ የፌዳራልና የክልል ትራንስፖርት አካላት አቅርቦ በማጸደቅ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

## 16. ቅጣትን ስለማስፈፀም፡-

በመላው አገሪቱ በመደበኛነት በመርሃ-ግብር ተደገፎ ከሚሰጠው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በላይ ከፍተኛ የሕዝብ ክምችት ሲኖርና የአቅርቦት እጥረት በሚፈጠርባቸው ጊዜያቶችና ቦታዎች እንዲሰጥ የሚደረገው የልዩ ጉዞ ፈቃድና አገልግሎት አፈጻጸም ውስጥ የሚከሰቱ የዲስፕሊን ጥፋቶችን በተመለከተ ስለሚወሰዱ ቅጣቶች በቅርቡ በተሻሻለውና ሥራ ላይ በሚውለው የሕዝብ

ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ሥራ ሂደት የሥምሪት አፈጻጸም አገራዊ መመሪያ ክፍል ዘጠኝ የተካተተ ሲሆን በዚሁ መመሪያ መሰረትም የቅጣት ውሳኔ ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡

## 17. *የልዩ ጉዞ መረጃን ስለማደራጀት፡-*

የሕዝብ ክምችትና የትራንስፖርት አገልግሎት ፍላጐት በሚኖርባቸው በዚህ መመሪያ በተዘረዘሩ ወቅቶች የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ በሁሉም ደረጃ ስለተሰጡ አገልግሎቶችና ስለአጠቃላይ የአፈፃፀም ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ የመያዝ የማደራጀትና በሪፖርትም ለሚመለከታቸው አካላት የማሳወቅ ግዴታና ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

## 18. *የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን፡-*

ይህ መመሪያ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ቀጥተኛ የተግባር ኃላፊነት ባለባቸው ትራንስፖርት ማኅበራት ትራንስፖርተሮችና አሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## 19. *መመሪያውን ስለማሻሻል፡-*

መመሪያውን ማሻሻል ሲያስፈልግ ወይም ሲታመንበት በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 20. *መመሪያው ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ፡-*

ይህ መመሪያ በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ከጸደቀበት ከመጋቢት 15 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምር ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

*ፌደራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን*

*መጋቢት 2005 ዓ.ም*

*አዲስ አበባ*